# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT** جبهة تحرير اورومو

Gaafa: 18/02/15
Date: تاريخ

Lakk.: 006/stm - abo/2015
No.: رقم

**በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያነጣጠረውን ኣደጋ መመከት የኦሮሞ ተወላጅ የዜግነት ግዴታ ነው!**

*(የፊንፊኔ “ማስተር ፕላን” ኣቅድን በተመለከተ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር የተሰጠ መግለጫ)*

ከኣንድ ምዕተ-ዓመት በላይ በኦሮሚያ ላይ የተዘረጋው የባርነት ኣገዛዝ በሺዎች የሚቆጠር የኦሮሞ ህዝብ ከቀዬውና ከመሬት ይዞታው ኣፈናቅሎ መሬት-ኣልባ ኣድርጎታል። የኢምፓዬሪቱን ከተማ በኦሮሚያ እምብርት ለማቋቋም ሲወሰድ በነበረው ከዘር-ማጥፋት (ጄኖሳይድ) ወንጀል ባልተናነሰ ደረጃ ሲወሰድ በነበረው እርምጃ ኣቢቹና ገላን የተባሉ የኦሮሞ ጎሳዎች ከኣካባቢው እንዲጠፉ ተደርገዋል። ``ሃገር ማቅናት`` በሚል መርህ ሲወደስ የነበረው ጠላታዊ እርምጃ በወያኔ የኣገዛዝ ዘመንም ``ልማትና እድገት`` በሚል ሽፋን በመቀጠሉ በኣሁኑ ወቅት ከቀዬውና ከኑሮው እየተፈናቀለ ያለው የኦሮሞ ዜጋ ቁጥር ከበፊቱ ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ ኣልታየም። የወያኔ መንግስት ከቀደሙት ጨቋኝ ገዢዎች የወረሰውን እቅድና ፖሊሲ ለማስቀጠል ላለፉት 23ዓመታት የኦሮሞ ኣርሶኣደሮችን እንደቦሌ-ቡልቡላ፣ ለገ-ጣፎ፣ ኣቃቂ፣ ሰበታ፣ ሱሉልታ፣ ቡራዩና ከመሳሰሉት ኣካባቢዎች በማፈናቀል መሬቱን ሲሸጥና ሲከፋፈለው ዛሬ መድረሱ የተሰወረ ኣይደለም።

የኦሮሞ ህዝብን በማይፈይደውና ከቀዬውና ከመሬቱ ኣፈናቅሎ ለድህነትና ጉስቁልና የሚዳርገውን የጨቋኝ ገዢዎች እቅድ በመቃወምም በርካታ የኦሮሞ ዜጎች የህይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። የታሰሩትና ከባድ ድብደባና ሰቆቃ የተፈጸመባቸው በብዙ ሺዎች ይቆጠራሉ። ለኦሮሞ ህዝብ መብት መከበር ሲሉ በጠላት የተገደሉትና ለእንግልት የተዳረጉት የኦሮሞ ዜጎች መስዋዕትነት የከፈሉበት ዓላማ በከንቱ እንዳይቀርና በኦሮሞ ላይ ያነጣጠረው ይህ የጠላት እቅድ እንዳይሳካ ማድረግ ዛሬም የያንዳንዱ የኦሮሞ ዜጋ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ገዢዎች እቅድና ፖሊሲ የኦሮሚያን ካርታ መቀየርና የኦሮሞን ህዝብ የሉዓላዊነትና የነጻነት ጥያቄ ለማፈን መሆኑ ከማንም የተሰወረ ኣይደለም። ለዚህም የኦሮሞ ህዝብ ከመጀመሪያ ኣንስቶ እስከዛሬ ድረስ ይህንን የጠላቶች ሴራ በጀግንነት በመጋፈጥ ለፍትህና ለመብቱ መስዋዕትነት ሲከፍል እንደነበር የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ሂደት ይመሰክራል። በኢትዮጵያ ገዢዎች በኦሮሞ ላይ ሲፈጸም ከዛሬ የደረሰውን ይህንን ተንኮልና ክፋትም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ሲታገለውና ሲያታግልበት እንደነበርና ኣሁንም እየታገለው መሆኑ ግልጽ ነው።

የፊንፊኔ ማስተር ፕላን በማለት የታቀደውን ይህንን ሴራ ኣስመልክቶ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ሊቀመንበር ኣቶ ዳውድ ኢብሳ ኣዲሱን ዓመት 2015ን ምክንያት በማድረግ ባስተላለፉት መልዕክት ''***የፊንፊኔ ማስተር ፕላን የሚባለው የቀደሙት የኢትዮጵያ መንግስታት ሲያደርጉት ከነበረው በተለየና ዘመናዊ መልክ በተላበሰ መልኩ የኦሮሞን ህዝብ ከመሬቱ በማፈናቀል ማንነቱን ማጥፋት ላይ ያነጣጠረ ነው***'' በማለት ከበስተጀርባው ያለውን ሴራ ኣጋልጠዋል።

የኦሮሚያን መሬትና ከተሞች ከኦሮሚያ ኣስተዳደር ስር በማውጣት በፌዴራል ኣስተዳደር ስር ኣስገብተው እንዳሻቸው ለመሸጥና ለመቀራመት ያለመውን ይህንን ጠላታዊ እቅድ በተመለከተ የወያኔ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣን የሆነው ኣባይ ጸሃዬ ሰሞኑን ባደረገው ንግግር ''***ለፊንፊኔ የወጣው እቅድ ስራ ላይ ይውላል! ይህንን የሚደናቀፉትን ሁሉ ልክ እናስገባቸዋለን! ማንነታችንን እናሳያቸዋለል!***'' በማላት በኦፒዲኦ ኣስተዳዳሪዎችና ሹማምንት ላይ ላይ ዝቷል። ኣምባገነኖች ሲፎክሩና ሲዝቱ እንደሚባረሩ የታወቀ ቢሆንም የዚህ የወያኔ ሹም ፉከራ ወያኔዎች ምን ያህል ህዝቡን እንደሚንቁና ምን ያህል እንደዘቀጡ ያሳያል። የኦሮሞን ህዝብ ከምድረ-ገጽ በማጥፋትና ለድሕነት በመዳረግ የተንደላቀቀ ኑሮ መኖር የለመዱት የኢትዮጵያ ገዢዎች የሚያሰሙት ፉከራና ዛቻ የኦሮሞን ህዝብ ለመብቱና ለማንነቱ ከመታገል ፈጽሞ ኣያግደውም። የኦሮሞ ህዝብም ይህ ስራ ላይ ይውላል በሚል የወያኔ ሹም የሚዝትበት እቅድ በማንነቱና በመብቱ ላይ ያነጣጠረ መሆኑን በይበልጥ ስለሚገነዘብ ነጻነቱንና ሉዓላዊነቱን ለመጎናጸፍ እያካሄደ ያለውን ትግል በማፋፋም ከግቡ የሚያደርስ መሆኑ ጥርጥር የለውም።

ስለሆነም የኦሮሞ ህዝብ ጠላት የሆነውን ስርዓት ለማገልገል ከወሰኑት የኦፒዲኦ ኣባላት ውጪ የምትገኙ የኦሮሞ ተወላጆች ኣባይ ጸሃዬ ያሰማው የንቀትና የተስፋ መቁረጥ ንግግር ጠላት መቸውንም ጠላት መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለሆነ፣ የኦሮሞን ህዝብ መብት ለማስከበር ከህዝባቸው ጎን በመሰለፍ እንዲታገሉ፣ በሚወስዱት ታሪካዊ እርምጃም ከታሪክ ተጠያቂነት እራሳቸውን እንዲያድኑ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በድጋሚ ወገናዊ ጥሪውን ያቀርብላቸዋል።

P.O. Box 6973 Asmara, Eritrea Tel 2911 110236 Email: Caalchis@gmail.com, *www.oromoliberationfront.org*

ከዚህም በተጨማሪ ለእኩልነት፣ ለዲሞክራሲና ለፍትሕ እንታገላለን የሚሉ ሁሉ የኦሮሞን ህዝብ የመኖር መብት እየነፈገ ያለው ኣርመኔያዊ የጠላትነት እርምጃ በይፋ እየተፈጸመ ባለበት በኣሁኑ ወቅት፣ ከማጋለጥና ከመቃወም ከዳር ቆሞ መመልከት ወይንም እንዳልሰሙ በዝምታ ማለፍ በታሪክ የሚያስጠይቅ መሆኑን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ኣጥብቆ ያሳስባል።

ይህንን የኦሮሞን ህዝብ ማንነት ማጥፋት ላይ ያነጣጠረውን የጠላት እቅድ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በጥብቅ እንደሚያወግዝና እንደሚያከሽፈው በድጋሚ ለመላው የኦሮሞ ህዝብ እየገለጸ፣ የህዝብን መብት የማያከብርና የሃገር ባለቤት የሆነውን ህዝብ የሚያጠፋ እቅድና ፖሊሲ በህዝብ ትግል የሚከሽፍ መሆኑ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር እምነት ነው።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**

**የካቲት 18 ቀን 2015ዓም**